# በህብረተሰብ ተሳትፎ የዓይን ማዝ በሽታን መቆጣጠር

## ለህብረተሰብ የጤና አጠባበቅ አገልግሎት የተዘጋጀ መመሪያ




በዓለም ጤና ድርጅት፣ በሄለን ኬለር ኢንተርናሽናልና በኤድና ማክኔል ክላርክ ፋውንዴሽን ተዘጋጅቶ
በካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ አማካኝነት ወደ አማርኛ ተተርጉሞ የቀረበ መመሪያ

ጥቅምት 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

Permission to publish online granted by The Carter Center, November 2006

# መቅድም

ዓይን ማዝ በሽታ ክላሚዲያ ትራኮማቲስ በተባለ ተህዋስ አማካኝነት የሚመጣ ሲሆን ተገቢው ህክምና በጊዜው ካልተደረገለት ወደ ዓይነ ስውርነት ሊያመራ የሚችል ነው::

ሳይንቲስቶች ስለበሽታው አምጪ ተህዋስ በቂ ጥናት ቢኖራቸውም፤ እንዲሁም የተላላፊ በሽታ ኤክስፐርቶች በበኩላቸው የበሽታውን ሥርጭት ሂደት ለመቆጣጠር ቢጥሩም በአሁኑ ጊዜ ዓይን ማዝን ለመቆጣጠር ተመራጭነት ያለው ሥልት ሆኖ የተገኘው ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን መንቀሳቀስ ነው:: ታዲያ ህብረተሰቡ ዓይን ማዝ የሚያስከትለውን ዓይነ ስውርነት ለመቀነስ በሚደረገው እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጥ እንዴት ሊበረታታ ይችላል? ይህን ጥያቄ ለመመለስና በዓይን ማዝ ቁጥጥር ህብረተሰቡ እንዲነሳሳ ለማድረግ በአካባቢው የሚሠሩ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ባለሙያዎችን ማሳተፍ ተመራጭነት እንዳለው ይታመናል::

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማም የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች ዓይን ማዝን ለመቆጣጠር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የህብረተሰቡን ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን ሥልቶች እንዲጨብጡ ለማድረግ ነው:: መመሪያው በተለይም ዓይን ማዝ እንደችግር ሆኖ በሚታይባቸው አካባቢዎች እንዴት ለይቶ ማወቅ፣ ማከምና መከላከል እንደሚቻል መረጃዎችን ያቀርባል::

ይህን መመሪያ በተለያየ መንገድ መጠቀም የሚቻል ሲሆን ስለዓይን ማዝ በሽታ በቂ ግንዛቤ ለማግኘትና ለሌሎች ሥልጠና ለመሥጠት ያግዛል:: በተጨማሪም መመሪያው በአንድ አካባቢ ዓይን ማዝ መኖሩን ለይቶ ለማወቅና በዓይን ማዝ ቁጥጥር እንዴት የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት እንደሚቻል ለማስገንዘብ ይረዳል::

መመሪያው ተተርጉሞ የቀረበው በዓለም ጤና ድርጅት የዓይነ-ሥውርነት መከላከያ ፕሮግራም፣ በሄለን ኬለር ኢንተርናሽናልና በኤድና ማኮኔል ክላርክ ፋውንዴሽን ትብብር ከተዘጋጀው ፅሁፍ ተወስዶ ሲሆን ይህም መመሪያ ዓይን ማዝ በስፋት በሚገኝባቸው በኢትዮጵያ ክፍሎች ጉልህ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለን እናምናለን::

ተሾመ ገብሬ

የካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ ዳይሬክተር

## የዝግጅት አማካሪው አስተያየት

በአሁኑ ጊዜ ዓይን ማዝን ለመቆጣጠር ዋነኛና ትክክለኛው ስልት ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ሁሉንም ያሳተፈ እንቅስቃሴ ማድረግ ነው::
መመሪያውም ከሚያሳያቸው ዋና ዋና አቅጣጫዎች ውስጥ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች ዓይን ማዝን ለመቆጣጠር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የህብረተሰቡን ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን ስልቶችና ብልሀቶች እንዲያዘጋጁ የሚያስችል ነው::

ይህ መመሪያ ለህትመትና አገልግሎት የበቃው የተለያዩ ሙያተኞች ባደረጉልን ቀና ትብብርና ተሳትፎ ነው:: መመሪያውን ለማዘጋጀት የተዋቀረው የአማካሪ ኮሚቴ የትርጉም፣ የኢዲቲንግና የስዕል ዲዛይን ተግባራቱን በሚገባ ካጠናቀቀ በኋላ የተለያዩ ባለሙያዎች የማሻሻያ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ተደርጓል::

በመሆኑም መመሪያውን በማዘጋጀትና በማቀናበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉት፤ በአለም ጤና ድርጅት፣ በሄለን ኬለር ኢንተርናሽናልና በኤድና ማኮኔል ክላርክ ፋውንዴሽን ድርጅቶች ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች፤ እንዲሁም በአማርኛ ተዘጋጅቶ ለህትመት ለማብቃት ከመነሻ ጀምሮ ሙያዊ አስተዋፅኦ ላደረጉት የአማካሪ ኮሚቴ አባላት ለሆኑት ለዶ/ር እንዳለ ወርቃለማሁና ለአቶ ዓለምነህ ቸርነት ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

እንዲሁም መመሪያውን ለማዳበር በርካታ የጤና፣ የትምህርትና የማህበራዊ ዘርፍ ባለሙያዎች ገንቢ አስተያየታቸውን የሰጡን በመሆኑ በዚህ አጋጣሚ ሁሉንም እናመሰግናለን::

በተለይም አቶ ተሾመ ገብሬ መመሪያው ተሻሽሎና ታርሞ አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ ላደረጉልን መልካም ትብብር ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን::

በተጨማሪም አቶ ተረፈ ወንድማገኝ፣ ወ/ሮ የሺና ወ/ት ምንትዋብ በትጋትና በጥሩ የፈጠራ ችሎታቸው ላደረጉት አስተዋጽዖ፣ እንዲሁም ይህን መመሪያ በማተም በተባበረን ለኢ.ዲ.ኤም የህትመት ድርጅት ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

ይህ መመሪያ በመላው ኢትዮጵያ በተለይም ዓይን ማዝ በስፋት በሚገኝባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች በሚደረገው የፀረ ዓይን ማዝ ዘመቻና እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው እንገምታለን::

ዶ/ር ግሩም ኃይሉ
የካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ አማካሪ

# ክፍል 1

## ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ምንድን ነው?

1.1 ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ምንድነው?
1.2. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን እንዴት መለየት ይቻላል?
1.3. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) እንዴት ይተላላፋል?
1.4. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ስርጭት

ዓይን ማዝ የዓይነ ስውርነት ዋነኛ መንስኤ ነው::



የዓይን ማዝ በሽታን መከላከልና በህክምናም ማዳን ይቻላል::

ስዕል 1. በዓለማችን ዓይን ማዝ የዓይነ ስውርነት ዋነኛ መንስኤ ነው::

# ክፍል - አንድ

## ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ

### 1.1. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ምንድነው?

ዓይን ማዝ (ትራኮማ) ተላላፊ የሆነ የዓይን በሽታ ሲሆን ለዓይን በማይታዩ ረቂቅ ተህዋሲያን ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው:: የዚህ በሽታ አምጪ ተህዋስ ክላሚዲያ ትራኮማቲስ በመባል ይታወቃል::


በሽታው በመጀመሪያ አካባቢ ምንም ምልክት ላያሳይ ቢችልም ቀስ በቀስ የመቆርቆር ስሜት፣ እንባ ማንባት፣ የዓይን መቅላት፣ ብርሃን ማየት መፍራት፣ የዓይን ቆሻሻ ፈሳሽ የመሳሰሉትን ምልክቶች ያሳያል:: በመጨረሻ ደረጃ ላይ የደረሰ ዓይን ማዝ ደግሞ የዓይን ቆብ ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ እንዲቀለበስ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የመቆርቆር ስሜትና የዓይን መስታወት መቁሰልን ያስከትላል::

ዓይን ማዝ በሕፃንነት የዕድሜ ክልል ዓይንን በተደጋጋሚ በማጥቃትና በመለብለብ በላይኛው የዓይን ቆብ የውስጠኛ ክፍል ላይ በዓይን የማይታዩ ቀጫጭን ጠባሳዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል:: የበሽታው ክስተት ሲደጋገም ጠባሳዎቹ እያደጉና የላይኛውን የዓይን ቆብ ወደ ውስጥ በመቀልበስ (Trichiasis) ሽፋሽፍቶቹ የዓይን ብራንፊን (Cornea) ይፈገፍጋሉ:: በዚህም ጊዜ የዓይን መስታወት ብርሃን አስተላላፊነቱን ስለሚያጣ ዓይነ ስውርነት ይከሰታል::

የዓይን ማዝ በስፋት በሚገኝባቸው አካባቢዎች ሕመሙ የሚጀምረው በሕፃንነት ሲሆን ዓይንን የመለብለብና የመቆጣት ስሜት በአብዛኛው የሚስተዋለው ትምህርት ቤት ባልገቡና ገና ትምህርት በጀመሩ የህፃንነት ዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙት ነው:: በአዋቂዎች በአብዛኛው ሕመሙ ከመቆየቱ የተነሳ ጠባሳ አውጥቶ ይገኛል:: በሕብረተሰቡ ውስጥ በሽታው የተስፋፋ ከሆነና ሕመሙ የተለመደ ከሆነ ግን በሕፃናትም ላይ ጠባሳው ሊስተዋል ይችላል::




ሥዕል ፪ ወደ ዓይነ-ስውርነት የሚያመራው
የዓይን ማዝ ቁልቁለት



ስዕል 3. በዓይን ማዝ ምክንያት የሚከሰተውን ዓይነ ስውርነት መከላከል ይቻላል።

## 1.2. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን እንዴት መለየት ይቻላል?

ዓይን ማዝ በሽታን ለመለየት የሚረዱ አምስት (5) ዋና ዋና ምልክቶች ያሉ ሲሆን አንድ ሕመምተኛ ከአንድ ምልክት በላይ ሊኖረው ይችላል። የዓለም ጤና ድርጅት ለህክምና ክትትል ይረዳ ዘንድ በሽታውን በደረጃ ከቀላል ወደ ከባድ መድቦ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል አስቀምጦታል።

የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸው የዓይን ማዝ ደረጃዎች

- **ቀላል የዓይን መለብለብ /መቆጣት/ ስሜት** (Trachomatous Inflammation Follicular, TF)

  ይህ በአብዛኛው ሕፃናት ላይ የሚስተዋል የመጀመሪያው የዓይን ማዝ ምልክት ነው:: የዓይን መቅላት፣ የዓይን በቆሻሻ መጣበቅ፣ ዓይንን ማሳከክና የሕመም ስሜት ሊያስከትል የሚችል ሲሆን ይህን ለማረጋገጥ በሚደረገው ምርመራ የላይኛው የዓይን ቆብ ተገልብጦ ሲታይ ጥቃቅን ነጭ ነጠብጣቦች (follicles) ይታያሉ::

- ከባድ የዓይን መለብለብ /የመቆጣት/ ስሜት (Trachomatous Inflammation Intense, TI)

  ይህ ሁለተኛው የዓይን ማዝ ደረጃ ሲሆን የላይኛው የዓይን ቆብ የውስጠኛ ክፍል ከመጠን በላይ ሲለበለብ /ሲቆጣ/ የሚከሰትና በዚሁ ቦታ የሚገኙት የደም ሥሮችን ለማየት የሚያስቸግርበት ደረጃ ነው::

- የጠባሳ መፈጠር (Trachomatous Scaring, TS)

  የላይኛው የዓይን ቆብ የውስጠኛ ክፍል በተደጋጋሚ በዓይን ማዝ በመጠቃቱ ምክንያት ጠባሳ ያወጣል:: በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች አሸዋና ነፋሳት ወደ አይናቸው እንደገባባቸው ያህል የመቆርቆር ስሜት ይሰማቸዋል:: በምርመራ ወቅት የመለብለብ፣ የመቆጣትና የመቅላት ምልክቶች ላይታዩ ይችላሉ፡ ነገር ግን የጠባሳውን ምልክት የሚያረጋግጥ ነጭ መስመር ይታያል::


- የዓይን ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ ማደግ (Trachomatous Trichiasis, TT)

  ይህ በአራተኛ ደረጃ የሚታይ ምልክት ሲሆን የላይኛው የዓይን ቆብ የውስጥ ክፍል ጠባሳ በመስራት የዓይን ሽፋሽፍትን ወደ ውስጥ በመቀልበስ የዓይን መስታወት ብሌንን እንዲፈገፍግ ያደርጋል::

  የዓይን ማዝ በተስፋፋበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ይህን ደረጃ የሚገነዘቡ በመሆናቸው የዓይን ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ ተቀልብሶ የዓይን መስታወትን ሲቆረቁር ለጊዜያዊ ዕረፍት ሲባል ሽፋሽፍቱን በተለምዶ በወረንጦ ይነቅሉታል:: ይህ ደግሞ ለተለያዩ ጉዳቶች ሊዳርግ ይችላል::

- የዓይን ብሌንሬን ብርሃን አለማስተላለፍ (Corneal Opacity)

  ይህ አምስተኛውና የመጨረሻው ደረጃና በቀላሉ መለየት የሚቻል ነው:: በዚህ ጊዜ ንፁህ ሆኖ መታየት ያለበት የዓይን ክፍል በነጭ የተሸፈነ ሆኖ ይታያል:: የዓይን ሽፋሽፍቶችም የዓይን ብሌንሬን መፋቃቸውን በቀጠሉና በቆዩ ቁጥር ጠባሳ በመፍጠር ብርሃን የማስተላለፍ ተግባሩን በማስተጓጎል ዓይነ ስውርነትን ያስከትላሉ::




ስዕል 4. የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸው የዓይን ማዝ ደረጃዎች

## 1.3. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) እንዴት ይተላለፋል ?


ትራኮማ ከሰው ወደሰው በተለይም በህፃናት ላይ በቀላሉና በተለያዩ መንገዶች የሚተላለፍ በሽታ ነው:: ከእነዚህም ውስጥ

ሀ. ትራኮማ ያላቸው ህፃናት በአብዛኛው ዓይናቸው የቀላ፣ ከዓይናቸው በሚወጣ የዓይናር (ቅምጥ) ዓይናቸውን ለመግለጥ የሚቸገሩና አንዳንድ ጊዜም ከአፍንጫቸው ፈሳሽ የሚወጣቸው ናቸው:: ከዓይን የሚወጣው ዓይናር (ቅምጥ) በሽታ አምጪውን ተህዋስ የያዘ ከሆነ በቀላሉ ወደ ጣትና ልብስ በመነካካት ይበከላል::

ለ. ዝንቦች የዓይን በሽታ አምጪ ተህዋሲያኑን ከአንድ በሽተኛ ሰው ወደ ሌላ ጤነኛ ሰው ዓይን በመውሰድ ያስተላልፋሉ፣ ያሰራጫሉ::

ሐ. ህፃናት አብረው ሲተኙ የበሽታው አምጪ ተህዋሱን በቀላሉ ወደ ጤነኛው ህፃን በቀጥታ ወይም በተበከለ ልብስ አማካኝነት ያስተላልፋሉ::

መ. ሴቶች አብዛኛውን ጊዜያችውን በቤት ውስጥ ከልጆች ጋር የሚያሳልፉ በመሆናቸው



ስዕል 5. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) ከሰው ወደ ሰው እንዴት እንደሚተላለፍ::

ከወንዶች የበለጠ ለዓይን ማዝ (ትራኮማ) የተጋለጡ ናቸው::

## 1.4. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ስርጭት

ዓይን ማዝ በተለይ በገጠሩ፣ የግልና የአካባቢ ንፅህና በሌላቸው፣ የውሃ እጥረት በሚከሰትባቸው፣ ደረቅ የአየር ንብረት ባላቸው፣ በገጠሩ በሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ በስፋት ተንሰራፍቶ ይገኛል:: በሀገራችን ኢትዮጵያም ችግሩ በስፋት ይታያል::

የበሽታውን ስርጭት እንዲባባስ የሚያደርጉት ምክንያቶች ከቦታ ቦታ የሚለያዩ ቢሆንም በአጠቃላይ የኢኮኖሚያዊ ኋላቀርነት በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሹ ነው:: ሃገራችን ኢትዮጵያም በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የኑሮ ደረጃ ኋላ ቀርና ብዙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚዘወተርባት ሀገር በመሆኗ ችግሩ የበለጠ የከፋ እንዲሆን አድርጎታል::

ሀ. የውሃ እጥረት

በተለይ በገጠሩ አካባቢ ውሃ ያለበት ቦታ ከመኖሪያ ቤት እርቆ በሚገኝበት፣ ሴቶች በቤት ውስጥ ካለባቸው ሃላፊነት አኳያ ጊዜ የሚወስዱ በመሆኑና የውሃ አቅርቦቱም በቂ ባልሆነበት ሁኔታ የፊት ንፅህናን በየቀኑ ለመጠበቅ አዳጋች ይሆናል::

ለ. የዝንቦች መኖር

በመኖሪያ ቤት አካባቢ የከብቶች ማደሪያ መኖርና የቆሻሻ አወጋገዱ አግባብ ባለው ሁኔታ ካልሆነ ለዝንቦች መራባት ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር በሽታው ከሰው ወደ ሰው የመተላለፉን ሁኔታ ያባብሰዋል::

ሐ. በተፋፈገ ሁኔታ መኖር

ህፃናት የበሽታ አምጪ ተህዋሱ ዋነኛ ምንጮች በመሆናቸውና በተፋፈገ ሁኔታ በሚኖሩበት ጊዜ በሽታ አምጪ ተህዋሱን በቀላሉ ወደ ሌላ ሕፃን የማስተላለፍና በበሽታውም በተደጋጋሚ የመጠቃት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል:: በዚህም ምክንያት በዓይን ማዝ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መውደቅ ሊከሰት ይችላል::

መ. ሌሎች

- ለማጌጥ ሲባል ዓይን ላይ የሚደረጉ ነገሮች፣ ጢስ፣ አቧራና ሌሎች የባህል ህክምናዎች አይን እንዲቆጣ ያደርጋሉ:: አይንም ሲቆጣ በሚታሽበት ጊዜ በሽታ አምጪ ተህዋሱን በእጅ በመንካት ወደ ሌሎች ለማስተላለፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል::
- ድህነትም ለሌሎች በሽታዎች እንደሚያጋልጠው ሁሉ ለዓይን ማዝም መተላለፍ እድል ይፈጥራል:: ይህም ሲባል ድህነት ካለ አነስተኛ የመኖሪያ ቤትና ተፋፍጎ መኖር፣ አነስተኛ ገቢ፣ በቂ ትምህርት አለመኖርና በመሳሰሉት ምክንያቶች በሽታው እንዲስፋፋ ያደርጋል::

# ክፍል 2


## ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል?

2.1. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን ለመቆጣጠር የሚረዱ አራት ዋና ዋና ተግባራት

2.2. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዋና ዋና መንገዶች (ማመንን) ዝርዝር ተግባራት

2.3. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በመቆጣጠር ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው?

2.4. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) ዋና ዋና ስልቶች የሚያሳዩ ሰንጠረዥ





ስዕል 6. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የሚረዱ ተግባራት


# ክፍል ሁለት

## ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል?

### 2.1. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን ለመቆጣጠር የሚረዱ አራት ዋና ዋና መንገዶች


ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚከተሉትን አራት ነጥቦች በሙሉ እንደ ዋነኛ መንገድ አድርጎ መጠቀም ያስፈልጋል:: እነዚህ መንገዶች በእንግሊዘኛው ምህፃረ ቃል (SAFE) የሚለውን ቃል ይፈጥራሉ:: የዚህ የእንግሊዘኛ ምህፃረ ቃል የአማርኛው አቻ ደግሞ (ማመንን) ይባላል:: የቃላቶቹም ፍቺ እንደሚከተለው ይሆናል::

**S**urgical Correction



**ማ** የዓይን ቆብን በቀዶ ሕክምና ማስተካከል (ማስቆረጥ)

**A** Antibiotic Application




**መ** የዓይን መድሐኒት ሳያቋርጡ መጠቀም

**F** Facial Cleanliness




**ን** የፊትን ንፅሕና መጠበቅ (ፊትን አዘውትሮ መታጠብ)·

**E** Environmental Sanitation



**ን** የአካባቢን ንፅሕና መጠበቅ












ስዕል. 7

## በቀላል የቀዶ ህክምና ማስተካከል




በዓይን ማዝ የሚከሰተውን ዓይነ ሥውርነት ለመከላከል አፋጣኝና የመጨረሻው አማራጭ የአይንን ብርሃን አሳላፊ /ብራንፊ/ እንዳይፈገፈግና የብርሃን አስተላላፊነቱ ተግባር እንዳይስተጓጎል በቀላል የቀዶ ህክምና ሽፋሽፍቶቹን ማስተካከል ነው::

ይህ የቀዶ ህክምና በቀላል ቦታ /በጤና ጣቢያና በመድሃኒት መስጫ ጣቢያዎች /ሊሰራ የሚችልና ብዙ የካበተ እውቀትና ልምድ የማይጠይቅ ነው::

የአይን እስፔሻሊስቶች፣ በዓይን ሕክምና የሰለጠኑ ነርሶችና በዓይን ሕክምና የሚሰሩ ረዳት የጤና ባለሙያዎች የቀዶ ህክምናውን ሊያከናውኑ ይችላሉ::

## ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት መጠቀም



የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ምልክት የሚታይባቸውንም በወቅቱ መለየትና ማከም ተገቢ ነው::

ሀ) ፊትን መታጠብና ዓይንን በንፅህና መያዝ፣

ለ) ቴትራሳይክሊን 1% ቅባት የሚባለውን ፀረ ባክቴሪያ መድሐኒት በሁለቱም ዓይን በቀን ሁለት ጊዜ ለስድስት ሳምንት ያህል መጠቀም በዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ምልክት ለሚታይባቸው ሰዎች ዋነኛ የሕክምና መርሆዎች ናቸው:: ፀረ ባክቴሪያ መድሐኒት የሆነው ቴትራሳይክሊን 1% ቅባት በበሽተኛው ዓይን በሚደረግበት ጊዜ የማጣበቅ ስሜት ያለው በመሆኑ ብዥ ማለትን ያስከትላል፤ ይህ ለትንሽ ደቂቃዎች ብቻ የሚቆይ ስለሆነ በመኝታ ጊዜ ቢደረግ ችግሩን ያቃልለዋል:: በቂ ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት ካለ የቤተሰቡን አባላት በሙሉ ማከም ጠቃሚ ይሆናል::

## የፊት ንፅህና መጠበቅ



የፊት ንፅህና በሚገባ ከተጠበቀ ከዓይን የሚወጣው ቆሻሻ ስለማይኖር ዝንቦች በሽታውን የማሠራጨት አጋጣሚ አያገኙም:: የፊት ንፅህናን ለመጠበቅ ሁልጊዜ አዘውትሮ መታጠብ ጠቃሚ ሲሆን ፊትን በንፅህና ለመያዝ መጠነኛ ውሃ ብቻ በቂ ነው::




## የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ

- የሕብረተሰቡ ሚና የግልና የአካባቢ ንፅህና እንዲሁም አመቺ የመኖሪያ ቤት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን፣ እነዚህም ውጤት የሚያመጡት በተቀናጀ የሕብረተሰብ እድገት ነው:: ምንም እንኳ ይህ በረጅም ጊዜ የሚመጣ ቢሆንም ዓይን ማዝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጉልህ ሚና አለው::

→ የእያንዳንዱ ቤተሰብ ሚና

ተገቢ የአየር ዝውውር ያለው ቤት ውስጥ በመኖር፣ ከመኖሪያ ቤት በተወሰነ ርቀት የሚገኝ የመፀዳጃ ቤት በመገንባትና በትክክል በመጠቀም እንዲሁም ቆሻሻን በአግባቡ በማስወገድና በማቃጠል የዝንቦች ቁጥርን ብሎም የበሽታው አምጪ ተህዋስ የመተላለፍ አጋጣሚን መቀነስ ይቻላል::

## 2.2. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዋና ዋና መንገዶች [(ማመንን) (SAFE)] ዝርዝር ተግባራት



ማ
በቀዶ ህክምና ማስተካከል



መ
ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት መጠቀም




ን
የፊትን ንፅህና መጠበቅ



ን
የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ

ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ መንገዶች ለመተግበር በርካታ ክንዋኔዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በመሆኑም እያንዳንዱ የህክምና ቡድን የትኛው መንገድ ለአካባቢው ህብረተሰብ ተገቢና የሚቻል መሆኑን ማጤን አለበት::

**ማ**በቀላል የቀዶ ህክምና
የላይኛውን የዓይን ሽፋሽፍት
**ማ**ስተካከል




**ይህ የቀዶ ህክምና ምንድነው?**

- ይህ የቀዶ ህክምና ቀላልና ውጤታማ ሲሆን የዓይን ብርሃን አስተላላፊ (ብራንፊ) በላይኛው የዓይን ሽፋሽፍት እንዳይፋቅ ያደርጋል፡፡
- የጤና መኮንኖች፣ ነርሶች፣ ጤና ረዳቶችና ሌሎች መለስተኛ የጤና ባለሙያዎች ቢሰለጥኑ የቀዶ ህክምናውን ማካሄድ ይችላሉ፡፡
- በማንኛውም በአቅራቢያ በሚገኝ ዝቅተኛ የጤና ድርጅት ሊከናወን ይችላል፡፡
- ከቀዶ ህክምናው በኋላ በድጋሚ የዓይን ሽፋሽፍቶቹ ተቀልብሰው እንደሆነ ለማየትና የህክምናውን ውጤት ለመከታተል ህሙማኑን ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ቀጠሮ ሰጥቶ ውጤቱን ማየት ያስፈልጋል፡፡

**የቀዶ ህክምናውን ለማካሄድ ምን ያስፈልጋል?**

- በቀዶ ህክምናው ከ2 እስከ 4 ሳምንት ባላነሰ ጊዜ የሰለጠነ ባለሙያ፣
- ለመረጃ አያያዝ መዝገብ ማዘጋጀት፣
- የቀዶ ህክምናውን ለመሥራት የሚያስፈልጉ የተለያዩ የህክምና መሣሪያዎች፣
- ለቀዶ ህክምናው የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮች ለምሳሌ መስፊያ ክርና የመሳሰሉት፣
- መድሃኒት፣
- ማደንዘገር፣
- ለህሙማን ማመላለሻ ትራንስፖርት /ተሽከርካሪ/ ያስፈልጋል፡፡

**መ**ልጆችንና ቤተሰብን
በፀረ ባክቴሪያ
**መ**ድሐኒት
ቴትራሳይክሊን 1% ቅባት
ማከም ፤

**የፀረ ባክቴሪያ መድሐኒት (ቴትራሳይክሊን 1% ቅባት) ምንነትና**
አወሳሰድ

- ቀላል (ከባድ) የአይን መለብለብ/መቆጣት (TF and TI) ያላቸውን ሕፃናት እንዲሁም የቤተሰብ አባላት በፀረ ባክቴሪያው መድሐኒት (ቴትራሳይክሊን 1% የዓይን



ቅባት) ማከም አስፈላጊ ሲሆን ይህም ሕክምና የሚሰጠው በቀን ሁለት ጊዜና ለስድስት ተከታታይ ሣምንታት ይሆናል፡፡

- የፊት ንፅህና በየጊዜው ካልተጠበቀ በስተቀር ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት የሆነውን /ቴትራሳይክሊን 1% ቅባትን/ ብቻውን መጠቀም ችግሩ እንዳይባባስ ለተወሰነ ጊዜ ይረዳል እንጂ ሙሉ ለሙሉ አይቀርፈውም፡፡ ስለዚህ ስለበሽታው መከላከያ መንገዶች በትክክልና በበቂ ሁኔታ ተገናዝቦ ለዘላቂ መፍትሄው የባህርይ ለውጥ ማምጣት ወሳኝነት አለው፡፡
- ሌላው የፀረ ባክቴሪያ መድሐኒት/ቴትራሳይክሊን/ ሕክምና አማራጭ አጠቃላይ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ማከም ሲሆን የመድሐኒት አሠጣጥ ፕሮግራሙ እንደየአካባቢው ሊለያይ ይችላል፡፡ እንዲሁም በተጨማሪ የበሽታው ምልክት የሚታይባቸውን ነዋሪዎች በመድሐኒቱ ማከም ተገቢ ነው፡፡

<u>ለሕክምናው የሚያስፈልጉ ግብአቶች</u>

- የሰው ሃይል
  እናቶች፣ መምህራን፣ ፈቃደኛ ግለሰቦች፣ የጤና ተጠሪዎች፣
- አስተዳደራዊ ቁሳቁስ፣
- የዕቃዎች ወጪ ገቢ መመዝገቢያ መዝገብ፣
- መሣሪያዎች
- የዕቃ መደርደሪያ /ማስቀመጫ/
- መድሐኒት (ቴትራሳይክሊን 1% ቅባት)
- መጓጓዣ፡- መድሃኒት ለማጓጓዣና ለሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎች

## ን የህፃናት ፊት ንፅህናን መጠበቅ



<u>የፊት ንፅህናን መጠበቅ</u>

- ምንም እንኳን የፊት ንፅህናን መጠበቅ ቀላል ቢመስልም የህብረተሰቡን የተወሳሰበ የአኗኗር ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ሲታይ አስቸጋሪ ነው:: ይኸውም ሴቶች ካለባቸው ተደራራቢ የሥራ ጫናና ለጉዳዩ ከሚሰጡት ትኩረት አንፃር ሲታይ ማለት ነው:: ሆኖም ግን ይህ አማራጭ በረጅም ጊዜ ሂደት ለግለሰቡ፣ ለቤተሰብም ሆነ ለህብረተሰቡ የሚሰጠው ጥቅም ቀላል አይሆንም::

ስለዚህ ወላጆች በዚህ ድርጊት ማመን፣ ጊዜያቸውን ለጉዳዩ ማዋልና ልጆቻቸውን ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

- ህፃናት እርስ በርስ እንዲረዳዱ ማድረግ፣ ታላላቅ እህቶችና ወንድሞች ታናናሾቻቸውን እንዲያስተምሩና እንዲረዷቸው ማስቻል ያስፈልጋል::
- በመዋለ ሕፃናትና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ሕፃናትን ስለፊት ንፅህና አጠ ባበቅ ትምህርት መስጠትና ማበረታታትም ተገቢ ነው::

<u>የሚያስፈልጉ ግብዐቶች</u>

የሰው ኃይል:-

ሴቶች፣ እናቶች፣ ወንዶች፣ የጤና ተጠሪና የትምህርት ቤት አስተማሪዎች ትምህርቱን በመስጠትና በማበረታታት ትልቅ ሚና አላቸው::

<u>ቁሳቁሶች:-</u>

ትምህርቱን ለመስጠት የሚረዱ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች /ፖስተርና የመሳሰሉት/ ያስፈልጋሉ::

## 7. የአካባቢ ንፅህናና ልማት



### የአካባቢን ንፅህናና ልማት ማጠናከር

- ግንባር ቀደም የጤና ባለሙያዎችና የጤና ተጠሪዎች እንዲሁም ሕብረተሰቡ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ለለውጥና ለልማት እንዲሰሩ ማድረግ፣
- በነዋሪዎችና በአካባቢው ባሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ትብብር የሚሰሩ የውሃና የአካባቢ ንፅህና ፕሮጀክቶችን ማጠናከር፣
- የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎችን መገንባት
- በቂ የአየር ዝውውር ያላቸውን ሽንት ቤቶች በመገንባት በዝንቦች የሚፈጠረውን ችግር መቀነስ፣
- ቆሻሻን በተገቢው ሁኔታ ማስወገድና
- የዝንቦችን መራቢያ ማስወገድ ተገቢ ነው::

### የሚያስፈልጉ ግብዐቶች

የሰው ኃይል:- የአካባቢ የሥራ ኮሚቴ ከየአገልግሎት ዘርፉ በማውጣጣት ማቋቋም፡ ኮሚቴው:- ቤተሰብ፣ ግለሰብ፣ የጤና ባለሙያ፣ የውሃ ባለሙያ፣ ፈቃደኛ ግለሰቦች፣ የሐይማኖት አባቶችን ያቀፈ ቢሆን ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል::

ስልጠና:- የአካባቢ የሥራ ኮሚቴዎችን እንዴት ማዋቅርና ማሠራት እንደሚቻል ስልጠና መስጠት፣


የግንባታ መሣሪያዎች:- ቧንቧ፣ ሲሚንቶ፣ አፈርና የመሣሠሉት እንዲሁም የመጓጓዣ አገልግሎቶች ያስፈልጋሉ::

## 2.3. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በመቆጣጠር ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው?

በሕብረተሰቡ ውስጥ የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን ለመቆጣጠርና ፕሮግራሙን ውጤታማ ለማድረግ ጥረቱን ከሁሉም የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር ማቀናጀት ተገቢ ነው:: የዓይን ጤንነትም በዋነኛነት በመሠረተ ጤና ክብካቤ አገልግሎት መካተት አለበት::

ለዚህም:-

- የመንግሥት በጉዳዩ የማመንና ትኩረትና ድጋፍ መስጠት ጉልህ ሚና አለው::
- የብሄራዊ ዓይነ ሥውርነት መከላከያ ፕሮግራም ካለ ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን ቁጥጥር አብሮ ማካሄድ
- ከሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ መስራትም ያስፈልጋል::
- ከሌሎች የጤና እንቅስቃሴዎች/ክትባት፣ የት/ቤቶች የጤና አጠባበቅ ትምህርት እና ከመሳሰሉት/ጋር አብሮ አቀናጅቶ መስራት ጠቃሚ ነው::

| በዓይን ማዝ (ትራኮማ) ቁጥጥር ተግባራት መሳተፍ የሚችሉ እነማን ናቸው? | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| **ቀላል የቀዶ ህክምና ለማካሄድ**<br>▪ ነርሶች<br>▪ ጤና ረዳቶች<br>▪ መለስተኛ የጤና ባለሙያዎች ወይም<br>▪ ሐኪሞች ያስፈልጋሉ | **ቤተሰብን በፀረ ባክቴሪያ ቴትራሳይክሊን 1% <u>ቅባት ለማከም</u>**<br>▪ የጤና ተጠሪዎች<br>▪ የዓይን ሕክምና ሠራተኞች ያስፈልጋሉ | **የሕፃናት ፊት <u>ንፅህናን ለመጠበቅ</u>**<br>እናቶች፣ አያቶች፣ አባቶች፣ ታላላቅ እህቶችና ወንድሞች እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ:: | **የውሃ አቅርቦትንና የአካባቢ ንፅህናን ለመጠበቅ**<br>▪ የጤና ኮሚቴዎች<br>▪ በህብረተሰቡ<br>• ውስጥ ያሉ የአመራር አካላት<br>▪ መንግስታዊ ተቋማት<br>▪ የፖለቲካ ሰዎች<br>▪ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያስፈልጋሉ:: |
| **የቀዶ ህክምናው ተጠቃሚዎችን የሚያበረታቱ <u>የህበረተሰቡ ክፍሎች</u>**<br>▪ ሕሙማን፣<br>▪ ዘመዶች፣<br>▪ የባህል ሕክምና አዋቂዎች፣<br>▪ የሕብረተሰቡ መሪዎች ህክምናው የሚያስፈልጋቸው ሰዎች በቅርብ ወዳለው የጤና ድርጅት እንዲሄዱ ሊያበረታቱ ይችላሉ:: | **ሕክምናውን <u>ለመከታተል</u>**<br>▪ እናቶች<br>▪ አባቶች<br>▪ ሴት አያቶችና<br>▪ ሌሎች ዘመዶች ድጋፍ በማድረግ ያግዛሉ:: | **የፊት ንፅህና አጠባበቅን በቀጣይነት <u>ለማበረታታት</u>**<br>▪ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል<br>▪ የጤና ባለሙያዎችና የልማት ሰራተኞች<br>▪ የትምህርት ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች<br>▪ ህጋዊ የባህል ሕክምና አዋቂዎችና<br>▪ የልምድ አዋላጆች<br>• ጉልህ ሚና አላቸው<br>▪ የሀይማኖት መሪዎች | **የአካባቢውን ሕብረተሰብ ተሳትፎ <u>ለማጎልበት</u>**<br>▪ የልማት ሠራተኞች<br>▪ የሴቶች ኮሚቴዎች<br>▪ የጤና ባለሙያዎች አጋዥ ሃይሎች ናቸው:: |

ስዕል ፰. በዓይን ማዝ ቁጥጥር ተግባራት መሳተፍ የሚችሉ የህብረተሰብ አባላት

## 2.4. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) ቁጥጥር ዋና ዋና ስልቶች የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | በቀላል ቀዶ ህክምና **ማ**ስተካከል (ማ) | ፀረ ባክቴሪያ **መ**ድሃኒት ቴትራሳይክሊን 1% ቅባት መጠቀም (መ) | የህፃናት ፊት **ን**ፅህናን መጠበቅ (ን) | የአካባቢን **ን**ፅህና መጠበቅና ጤናማ ማድረግ (ን) |
|---|---|---|---|---|
| ማወቅ የሚገባዎት መረጃ/ነጥብ | ▪ የላይኛው የዓይን ክዳን በመሸብሸብ የሽፋሽፍቶቹ ወደ ውስጥ መቀልበስና (Trichiasis) የዓይን ብሌንፌ በሽፋሽፍቶቹ መፋቅ፣<br>▪ ቀዶ ህክምናው እንዴት መካሄድ እንዳለበትና<br>▪ የጤና ባሙያዎች እንዴት መሠልጠን እንዳለባቸው:: | ▪ ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን ደረጃዎች ማወቅ፣<br>▪ ቀላልና ከባድ የዓይን መለብለብ/መቆጣት/ ለይቶ ማወቅና<br>▪ ሌሎች የሕክምና አማራጮችን ማወቅ | ▪ አስፈላጊነቱን፣<br>▪ የሕፃናት ፊት ንፅህና መጠበቅና ሁልጊዜ እንዲታጠቡ ማድረግ አስቸጋሪ እንደሆነ፣<br>▪ የጤና ባለሙያዎች እንዴት መሰልጠን እንዳለባቸውና<br>▪ ሰዎች እንዴት ሊነሳሱና ባህሪያቸውን ሊቀይሩ እንደሚችሉ:: | ▪ የውሃ አቅርቦት የት እንደሚገኝና ምን እንደሆነ ማወቅ፣<br>▪ የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ፣<br>▪ ተባባሪዎችን ለይቶ ማወቅ<br>▪ የሽንት ቤት አሠራርን ማወቅ (የሚሰራው ሽንት ቤት በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖረው ማድረግ) |
| ማድረግ የሚገባዎት ነጥብ | ▪ የአይን ክዳን አፕሬሽንን /የቀዶ ህክምናውን/ እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል መማር፣<br>▪ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን ማሟላትና<br>▪ አፕሬሽኑ የሚያስፈልጋቸውን ህሙማን ከሕብረተሰቡ ጋር በመሆን ለይቶ ማውጣት | ▪ ቴትራሳይክሊን የሚያስፈልጋቸውን ሕሙማን ለይቶ ማወቅ (ቀላልና ከባድ መለብለብ ያለባቸውን)፣<br>▪ ለህብረተሰቡ ስለችግሩ ማስረዳት፣<br>▪ ቴትራሳይክሊን ቅባት መስጠትና<br>▪ በየ3ና 6 ወሩ ክትትል ማድረግ | ▪ ግንባር ቀደም የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠን፣<br>▪ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ማሳተፍና<br>▪ ሴቶችን ማሳተፍ:: | ▪ በህብረተሰቡ ውስጥ በአመራር ደረጃ ካሉ ሰዎች ጋር መወያየት፣<br>▪ ከሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር የትራኮማ ቁጥጥር ፕሮግራምን እንዴት አቀናጅቶ ማካሄድ እንደሚቻል፣<br>▪ በውሃ አቅርቦት የአካባቢን ንፅህና እንዲሻሻል ማበረታታት፣ |

| | ቀላል ቀዶ ህክምና ማካሄድ | ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት ቴትራሳይክሊን 1% ቅባት መጠቀም | የህፃናት ፊት ንፅህናን መጠበቅ | የአካባቢን ንፅህና መጠበቅና ጤናማ ማድረግ |
|---|---|---|---|---|
| ሕብረተሰቡ ማወቅ ያለበት ነጥብ | ▪ ቀዶ ህክምናው ቀላልና ሌላ መዘዝ የማያስከትል መሆኑን፣<br>▪ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተከናውኖ እንደሚያልቅና የ15 ደቂቃ ጊዜ ብቻ የሚወስድ ህክምና መሆኑን፣<br>▪ ቀዶ ህክምናው ውጤታማ እንደሆነና<br>▪ በቀዶ ህክምናው ዓይነሥውርነትን መከላከል እንደሚቻል:: | ▪ በሽታው በአብዛኛው ሕፃናትን እንደሚያጠቃ፣<br>▪ የቴትራሳይክሊን ቅባቱ እንዴት በዓይን እንደሚደረግ፣<br>▪ መድሃኒት ብቻውን በቂ እንዳልሆነና ለሌሎች ስልቶችም እገዛ ማድረግ እንደሚያስፈልግና<br>▪ በባለሙያዎች በታዘዘው መሠረት መድሃኒቱን መስጠት | ▪ የፊት ንፅህናን መጠበቅ ትራኮማን እንደሚከላከልና<br>▪ በአነስተኛ ውሃ የብዙ ህፃናት የፊት ንፅህናን መጠበቅ እንደሚቻል:: | ▪ የውሃን አስፈላጊነት<br>▪ ዝንቦች እንዴት ዓይን ማዝን (ትራኮማ) እንደሚያስተላልፉና<br>▪ ዝንቦችን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል:: |
| ሕብረተሰቡ ማድረግ የሚገባው ድርጊት | ▪ ለቀዶ ህክምናው መምጣትና ክትትል ማድረግ<br>▪ አረጋውያንን ማገዝና ለቀዶ ህክምናው እንዲመጡ ማበረታታት | ▪ የቴይራሳይክሊን 1% ቅባት በቀን ሁለት ጊዜ ለስድስት ተከታታይ ሳምንታት ማድረግ<br>▪ ለአንዱ ሰው የተሰጠውን መድሐኒት ለሌላው አለመጠቀም | ▪ የልጆች ፊት በየጊዜው ንፁህ ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ፣<br>▪ ቤተሰቦች ልምዳቸውን ለሌሎች ማካፈልና<br>▪ የውሃ እጥረት ባለበት ቦታ ውሃ የሚቆጥቡ ቀዳዳ ያላቸውን ጣሳዎች ዛፍ ላይ ሰቅሎ መጠቀም:: | ▪ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎችን መገንባት፣<br>▪ በቂ የዓየር ዝውውር ያላቸውን ሽንት ቤቶች መገንባትና በትክክል መጠቀም<br>▪ ቤትንና አካባቢን ንፁህ ማድረግ |

# ክፍል 3

## ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን በህብረተሰቡ ተሳትፎ መለየት


3.1. ዓይን ማዝ (ትራኮማ) ያለባቸውን ሰዎች ለይቶ ለማውጣት ከህብረተሰቡ ጋር የሚደረግ ውይይትና ተግባራት፣

3.2. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ በመንደሩ ውስጥ ችግር መሆኑን ማወቅ፣

3.3. ዓይን (ትራኮማ) ማዝ በሽታን ለመቆጣጠር የህብረተሰቡ ተሳትፎና ድጋፍ እንዴት እንደሆነ ለይቶ ማወቅ፣

3.4. የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን ለመቆጣጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ የሌሎች አጋሮችን ተሳትፎ መለየት፣

ዓይን ማዝ በሽታን ከህበረተሰቡ ጋር በመሆን መለየት



**ዓይን ማዝ በሽታን ለመለየት ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ሁሉንም አማራጮች መወያየት፣ መመርመርና ለይቶ ማውጣት ያስፈልጋል::**

ስዕል 9. ዓይን ማዝ በሽታን ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ለይቶ ለማውጣት የሚረዱ አራት ዋና ዋና መንገዶች

# ክፍል ሦስት

## ዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታን በህብረተሰቡ ተሳትፎ መለየት

### 3.1 ዓይን ማዝ (ትራኮማ) ያለቸውን ሰዎች ለይቶ ለማውጣት ከሕብረተሰቡ ጋር የሚደረግ ውይይትና ተግባራት፣

በሕብረተሰቡ ውስጥ ዓይን ማዝ ያለባቸውን ህሙማንን ለይቶ ለማውጣት መደረግ ያለበት የጀመሪያው ደረጃ ቢኖር በአካባቢው ያሉ የጤና ባለሙያዎችንና ሕብረተሰቡን ማሳተፍ ነው። በጤና ድርጅቶች የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች በተዋረድ ያሉትን የጤና ባለሙያዎችና ነዋሪዎቹን በማሳተፍ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። ይህ አካሄድ ደግሞ የህብረተሰቡን ድጋፍ ለማግኘት ያስችላል።

<u>ስለዓይን ማዝ በሽታ ለማወቅ ከህብረተሰቡ ጋር የሚደረግ ውይይትና ተግባራት</u>

ሀ. የዓይን ማዝ በሽታ የአካባቢው ህብረተሰብ ችግር መሆኑን ማረጋገጥ፣

ተግባር፡- በአካባቢው ካሉ የጤና ባለሙያዎችና ከአመራር አካላት ጋር በመሆን መወያየትና በአዋቂ ሴቶች ላይ የሽፋሽፍት መቀልበስ መኖሩን ማየት፣

ለ. የዓይን ማዝ በሽታ ምልክቶች ቀላልና ከባድ የዓይን የመለብለብ ስሜት ያላቸውንና እድሜያቸው ከ 4-7 ዓመት የሆኑትን ለይቶ ማውጣት፣

ተግባር፡- ህፃናትን መመርመር


ሐ. የዓይን ማዝ በሽታን ለመቆጣጠር የምንጠቀምባቸውን አራቱን ዋና ዋና መንገዶች (ማመንን) ግለሰቦችና ቤተሰቦች ተቀብለውት በፍቃደኝነትና በፍላጎት እገዛ እንደሚያደርጉ ማወቅ፣

ተግባር፡- ህብረተሰቡን ሊወክሉ ከሚችሉ አባላት ጋር መወያየት፣

መ. የዓይን ማዝ በሽታን ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት የሌሎች ተሳትፎ ሊኖር ስለመቻሉ ማጤን፣

ተግባር፡- የመንደሩን አመሰራረትና አወቃቀር የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ወይም ቀደም ሲል የተዘጋጀ ካለ መጠቀም ያስፈልጋል።

ማሳሰቢያ፡- የመጀመሪያዎቹ ሁለት ተግባራት በወረዳ ጤና ድርጅቶች የሚገኙ ባለሙያዎችን ተሳትፎ የሚጠይቁ ሲሆን የመጨረሻዎቹ ሁለት ተግባራት ግን በአካባቢው ባሉ ግንባር ቀደም የጤና ባለሙያዎችና የጤና ተጠሪዎች እንዲሁም በህብረተሰቡ አባላት ሊካሄዱ ይችላሉ።




በአካባቢው ካሉ የጤና ባለሙያዎችና መሪዎች ጋር መወያየትና እንደዚሁም በዓዋቂ ሴቶች ላይ የሳይኛው ሽፋሽፍት መቀልበስ መኖሩን ማየት

ህፃናትን መመርመር

ከህብረተሰቡ ተጠሪዎች ጋር መወያየት

የአካባቢውን ካርታ ማዘጋጀት

**ስዕል 10**

## 3.2. ዓይን ማዝ በሽታ በመንደሩ ውስጥ ችግር መሆኑን ማወቅ፣

በአንድ በተወሰነ አካባቢ የዓይን ማዝ በሽታ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የተሻለው መንገድ አጠቃላይ ቅኝት ማካሄድ ነው:: ምንም እንኳን የበሽታውን ደረጃ የሚያመለክት ጠለቅ ያለና ሙያን የሚጠይቅ ጥናት ለማካሄድ ባይቻልም ቀለል ባሉ በሁለት አስፈላጊ መንገዶች ጥናቱን ማካሄድ ይቻላል:: ይኸውም ከአካባቢው የጤና ተጠሪዎችና ከአመራር አካላት ጋር በመነጋገር የላይኛው ሽፋሽፍት የተቀለበሰባቸውን አዋቂ ሴቶች ለይቶ ማውጣት ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ህፃናትን ለዓይን ማዝ ምልክቶች መመርመር ይቻላል::

ተግባር 1:- በአካባቢው ካሉ የጤና ሠራተኞችና ከህብረተሰቡ ተጠሪዎች ጋር በመሆን መወያየት፣

ዓይን ማዝ በሽታ ወደ ዓይነ ስውርነት ማምራቱን ለማወቅ የሚያግዙትን ሁኔታዎች በጋራ በመሆን በትክክል መወያየት ይገባል:: ከእነዚህም ሁኔታዎች መካከል በአካባቢ የውሃ እጥረትና የዝንቦች መኖር እንዲሁም ተፋፍጎ መኖር ጥቂቶቹ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪ በአዋቂ ሴቶች ላይ የላይኛው ሽፋሽፍት መቀልበስ ያላቸውን ሰዎች መለየት ያስፈልጋል:: የሚከተሉት ጥያቄዎች

ስዕል 11.



| ጥያቄዎች | | | |
|---|---|---|---|
| ጥያቄ ሀ | የውሃ እጥረት አለን? | 1 አለ | 2 የለም |
| ጥያቄ ለ | በህፃናት ፊት ላይ ብዙ ዝንቦች ይታያሉን? | 1 ይታያሉ | 2 አይታዩም |
| ጥያቄ ሐ | ተፋፍጎ መኖር አለን? ብዙ ህፃናትስ በአንድ አልጋ ላይ ይተኛሉን? | 1 አዎን | 2 አይደለም |
| ጥያቄ መ | ለላይኛው ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ መቀልበስ ህብረተሰቡ የሚጠቀምበት የአካባቢ ቋንቋ አለን? | 1 አለ | 2 የለም |
| ጥያቄ ሠ | የላይኛው ሽፋሽፍታቸው ወደ ውስጥ የተቀለበሰባቸው አዋቂዎች/ልጆች በአካባቢው አሉ? ካሉ ሰዎቹን ለማወቅና በተግባር ለማየት ሙከራ ማድረግ ይገባል | 1 አሉ፤ ይገባል | 2 የሉም፤ አይገባም |
| ጥያቄ ረ | የላይኛው የዓይን ሽፋሽፍት የተቀለበሰበት ሰውን አይተዋል? | 1 አይቻለሁ | 2 አላየሁም |

ተግባር 2:- የዓይን መቆጣት ስሜት ያላቸው/የሚያሳዩ አይን ማዝ ህሙማን የሆኑ ህፃናትን በምርመራ ማየት፣

እድሜያቸው ከ4-7 ዓመት የሆኑ ህፃናትን በመመርመርና የዓይን ማዝ ቀላልና ከባድ የመለብለብ ስሜት /መቆጣት/ ያላቸውን (TF and/or TI) በመለየት ከሃምሳ ህፃናት መካከል አስሩ እንደተገኙባቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ምርመራውን እንዴት ማካሄድ ይቻላል?

- የላይኛውን የዓይን ክዳን እንዴት መገልበጥ እንደሚቻልና የዓይን ቀላልና ከባድ የመለብለብ ስሜትን (Trachomatis follicular, TF) እና (Trachomatis intensive, TI) እንዴት መለየት እንደሚቻል ለአካባቢው የጤና ተጠሪዎች ማስተማር፣
- ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ወደ መዋለ ህፃናት በመሄድ እድሜያቸው ከ4-7 ዓመት የሆኑትን ህፃናት ማሰባሰብ፣
- ከአካባቢው የጤና ተጠሪዎች ጋር በመሆን የ50 ህፃናትን ዓይን መመርመር፣
- ሁለቱንም ዓይን መመርመርና ምልክቱ በአንድ ዓይን እንኳን ከታየ መመዝገብና ማከም፣
- የምዝገባው ቅጽ በቀጣዩ ገፅ ላይ የቀረበ ሲሆን በምርመራ የተገኘውን ውጤት ለመመዝገብ የሚያስችል ነው::




ስዕል 12. ሃምሳ የሚሆኑና እድሜያቸው ከ4-7 ዓመት ከሆኑት ህፃናት ውስጥ የዓይን ማዝ ያላቸውን ለመለየት በመንደር ውስጥ ወይም በት/ቤት መመርመር

<u>ማሳሰቢያ:-</u>

- በምርመራ ወቅት የዓይን መለብለብ /መቆጣት ስሜት ያላቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ማዳረስ የሚያስችል መድሃኒት መኖር አለበት::
- የዓይንን መለብለብ /መቆጣት/ ስሜት ያላቸውን ህፃናት ወደፊት መከታተል እንዲቻል ስማቸውን በትክክል መመዝገብ ያስፈልጋል::
- ለአካባቢው የጤና ተጠሪዎች መድሃኒቱ እንዴት በዓይን እንደሚጨመር ማሳየት ያስፈልጋል::
- ምርመራ ከተደረገላቸው 50 ህፃናት መካከል አስሩ ካለባቸው በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ መታከም እንዳለባቸው የሚጠቁምና ከህብረተሰቡ፣ ከአመራር አካላት፣ ከቤተሰቦችና ከመምህራን ጋር በመሆን እንዴት በሽታውን መቆጣጣር እንደሚቻል በጋራ መምከር እንደሚያስፈልግ የሚያሳይ ነው::

## <u>የመመዝገቢያ ቅጽ</u>

ምርመራው የተካሄደበት መንደር/ቀበሌ/ትመህርት ቤት ስም ____________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ምርመራውን ያካሄደው የወረዳው የጤና ድርጅት የጤና ባለሙያ ስም ____________________

________________________________________

ምርመራውን ያካሄደው የአካባቢው የጤና ተጠሪ ስም ____________________

________________________________________

ሁለቱንም ዓይን በመመርመር ቀላልና ከባድ የዓይን መለብለብ /መቆጣት/ ስሜት ያላቸውን ህፃናትና ቤተሰቦቻቸውን በቴትራሳይክሊን ዓይን ቅባት በማከም የተገኘውን ውጤት በሚከተለው ቅጽ መሰረት መመዝገብ ያስፈልጋል::

| ተራ ቁ. | የህፃኑ/ኗ ስም | ቀላል የዓይን መቆጣት ስሜት(TF) ያላቸው | ከባድ የዓይን መቆጣት ስሜት(TI) ያላቸው | ሁለቱም ስሜቶች ያላቸው |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | | | | |
| 7 | | | | |
| 8 | | | | |
| 9 | | | | |
| 10 | | | | |
| 11 | | | | |
| 11 | | | | |
| 12 | | | | |
| 13 | | | | |
| 14 | | | | |
| 15 | | | | |
| 16 | | | | |
| 17 | | | | |
| 18 | | | | |
| 19 | | | | |
| 20 | | | | |
| 21 | | | | |
| 22 | | | | |
| 23 | | | | |
| 24 | | | | |
| 25 | | | | |
| ምርመራ ከተደረገላቸው 50 ህፃናት መካከል አስር ያህሉ የዓየን መቆጣት ስሜት አላቸው? አላቸው _______ የላቸውም ______ | | | | |

## 3.3. ዓይን ማዝ በሽታን ለመቆጣጠር የህብረተሰቡ ተሳትፎና ድጋፍ እንዴት እንደሆነ ለይቶ ማወቅ፣

የዓይን ማዝ በሽታን ለመቆጣጠር ህብረተሰቡ ምን ማድረግ እንዳለበት ከመናገር ይልቅ ሊጫወቱት ስለሚችሉት ሚናና ስለፈቃደኝነታቸው በማወያየት ከራሳቸው አንደበት መገንዘብ ያስፈልጋል:: በዚህም መሰረት ከህብረተሰቡ ጋር ስለ አራቱ ዓይን ማዝ በሽታ የመቆጣጠሪያ ስልቶች በመወያየት በምን ዓይነት ሁኔታ መሳተፍ እንደሚችሉ ሃሳባቸውን መቀበል ይገባል::



ስዕል 13.

በውይይቱ ሂደት በአካባቢው ጤና ድርጅት የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች እራሳቸው በቀጥታ ሊሳተፉ ይችላሉ:: አለበለዚያ ደግሞ ሃሳቡን ለአካባቢው የጤና ተጠሪ በማብራራት ከህብረተሰቡ ጋር እንዲወያይ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል::

### ተግባር 3:- ከህብረተሰቡ ጋር ውይይት ማድረግ

- የተለያዩ ፆታ፣ እድሜና የትምህርት ደረጃ ያላቸውን የአካባቢውን ህብረተሰብ ማወያየት፣ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለምሳሌ፣ ታዋቂ ግለሰቦችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ የጤና ባለሙያዎችን፣ የጤና ተጠሪዎችና የባህል ህክምና አዋቂዎችን ማነጋገር፣
- ለውይይት የሚጋብዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ለምሳሌ፣ ብዙውን ጊዜ የልጆቻችሁን ዓይን ንፅህና ትጠብቃላችሁን ብሎ መጠየቅ አዎንታዊ ምላሽ ያለውና አዎን ወይም አይደለም ከሚለው መልስ በላይ የማያስኬድ በመሆኑ ከዚህ ይልቅ የልጆችን ፊት በማጠብ በኩል ችግር አለ ወይ ተብሎ ቢጠየቅ ብዙ ያወያያል::
- አንዳንድ ሰዎች የተናገሩት ነገር በሙሉ ሲመዘገብ ሲያዩ የጭንቀት ስሜት ሊፈጥርባቸው ስለሚችል የውይይቱን ነጥቦች በማስታወስ ከውይይቱ በኋላ ሃሳቦቹን ማስፈር የተሻለ አማራጭ ነው::

<u>የውይይት መመሪያ</u>

**ማ**→ ሰዎች የዓይን ቆብ በቀዶ ህክምና **ማ**ስተካከልን ይቀበሉታል?

- ወደታችና ወደውስጥ የተቀለበሱ የላይኛው ሽፋሽፍትን ለማስወገድ ሰዎች ምን ያደርጋሉ?
- ሰዎች በዚህ ችግር የሚከሰተውን ዓይነ ስውርነት በቀዶ ህክምና መከላከል ይቻላል ብለው ያምናሉ?
- ስለ ዓይን ቆብ ቀዶ ህክምና ሰዎች ያውቃሉ?
- ዓይነ ስውርነትን ለመከላከል በሚደረገው ቀዶ ህክምና ሰዎች ይስማማሉ? ፍቃደኞስ ይሆናሉ?

- ቀዶ ህክምናው በምን ቦታ ቢሰራ ይመርጣሉ?
- ከህብረተሰቡ መካከል ቀዶ ህክምናው የሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዲመጡ የሚያሳምኑ፣ የሚያበረታቱ እነማን ናቸው? የባህል ህክምና አዋቂዎች ናቸው? አዛውንቶች ናቸው? መምህራን ናቸው?

**መ**→ ፀረ ባክቴሪያ **መ**ድሃኒትን ይጠቀማሉ?

- ለዓይን ማዝ ህክምና የአካባቢው ህብረተሰብ ባህላዊ መንገድ ይጠቀማል?
- የቴትራሳይክሊን ዓይን ቅባት በአካባቢው አለ?
- አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለመግዛት ፈቃደኞች ናቸው?
- የቴትራሳይክሊን ቅባቶችን በማይበላሽ መልኩ ለማከማቸት የሚቻለው የት ነው?
- የቴትራሳይክሊን ቅባትን በመጠቀም ረገድ የሰዎች ተሞክሮስ ምን ይመስላል?
- የዓይን ማዝ በሽታን ለማከም የቴትራሳይክሊን ቅባትን ለምን ያህል ጊዜ መጠቀም አለብን ብለው ያስባሉ?

**ን**→ የፊት **ን**ፅህናን መጠበቅ

- ዝንቦች ህፃናት ፊት ላይ እንዳያርፉ ምን ይደረጋል?
- የህፃናትን ፊት ንፅህና ለመጠበቅ ምን እየተደረገ ነው?
- የህፃናትን ፊት ንፅህና የበለጠ ለማሻሻል ምን ያደርጋሉ?
- ሰዎች ውሃ ለማግኘት ምን ያህል ይጓዛሉ?
- የውሃውን አጠቃቀም ከቤተሰቡ አባላት የሚወስነው ማነው?
- የፊት ንፅህናን ለመጠበቅ ምን ያህል ውሃ ያስፈልጋል?

**ን**→ የአካባቢያቸውን **ን**ፅህና ይጠብቃሉ?

- የውሃ አቅርቦቱ ምን ይመስላል?
- ስለ መፀዳጃ ግንባታና አጠቃቀም የህብረተሰቡ አመለካከት ምን ይመስላል?
- የቤት እንስሳት ከመኖሪያ ቤት አንፃር የት ይኖራሉ?
- የቤት ውስጥ ለውጥን በተመለከተ የሚወስነው ማነው?
- በህብረተሰቡ ውስጥ ለሚደረገው ለውጥ ኃላፊውና ውሳኔ ሰጪው ማነው?
- የህብረተሰቡ አባላት በሚደረገው የአካባቢ ለውጥ የአካባቢ ንፅህናና የውሃ አቅርቦት/ተባባሪ ይሆናሉ?
- በየቦታው መጸዳዳት የሚያስከትለውን ችግርና በዓይነ ምድር ምክንያት በሽታ መዛመት እንደሚችል ያውቃሉን?

## የውይይቱ ማጠቃለያ ቅጽ

ከውይይቱ ምን ውጤት ተገኘ?

ሀ በቀዶ ህክምና ማስተካከል ላይ ሰዎቹ የነበራቸው ግንዛቤ፣ ሃሳብና ፍርሃት፣

-
-
-

ለ በፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት /የቴትራሳይክሊን የዓይን ቅባት/ ላይ ሰዎቹ የነበራቸው ግንዛቤ እና ልምድ

-
-
-

ሐ የህፃናት ፊት ንፅህናን መጠበቅ ምን ያህል ከባድ ወይም ቀላል ነው ብለው ያስባሉ?

-
-
-

መ ህብረተሰቡ ለአካባቢው ንፅህናና መሻሻል የበኩሉን ድጋፍ እንዲሰጥ ማድረግ ምን ያህል አስቸጋሪ ወይም ቀላል ነው?

-
-
-

## 3.4. ዓይን ማዝ በሽታን ለመቆጣጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ የሌሎችን አጋሮች ተሳትፎ መለየት

በአካባቢው ያሉ ሌሎች ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎችን ለይቶ ማወቅ የዓይን ማዝ የቁጥጥር ሥራን ከጤና ትምህርት፣ ሃይማኖትና ከማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ጋር ለማቀናጀት ይረዳል:: ይህን መረጃ ለማግኘት ደግሞ ካርታዎች ጠቀሜታ አላቸው::

በተዋቀሩት ማህበራዊ ተቋማት/ ጤና፣ ትምህርት፣የሃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማህበራዊ ስብስቦች/ ጋር በጋራ መስራቱ ጠቀሜታ አለው::

### ተግባር 4 ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ተቋማቱን ለመለየት የሚረዳ ካርታ ማዘጋጀት፣

**እንዴት ማዘጋጀት ይቻላል?**

ብዙ የሚመዘገቡና መታየት ያለባቸው ነገሮች ስለሚኖሩ በመጀመሪያ ካርታውን በመሬት ላይ ማስቀመጥ ወይንም በሲሚንቶ ምንጣፍ ላይ በቾክ መሳልና በኋላ በወረቀት ላይ ማስፈር ይቻላል::



ስዕል 14.

## በካርታው መስፈር ያለባቸው

### የመንደሩ አጠቃላይ አቀማመጥ

- ቤቶች፣
- ሜዳዎች
- የደን ቦታዎች፣
- የውሃ መገኛ ምንጮች
- የመኪናና የእግረኛ መንገዶች፣
- የመሰብሰቢያ ቦታዎች፣
- የመንደሩ አጠቃላይ ነዋሪ ብዛት፣

### የመንደሩ የጤና ተቋማት

- ክሊኒክ/የመድኃኒት መሸጫና ጤና ጣቢያ አቅጣጫ የሚያሳይ ቀስት ፣
- በቅርበት የሚገኙ ሆስፒታሎች አቅጣጫ የሚያሳይ ቀስት፣
- የጤና ባለሙያው የሚኖርበት ቦታ
- የባህል ህክምና አዋቂው የሚኖርበት፣
- የልምድ አዋላጇ የምትኖርበት፣
- የተንቀሳቃሽ የጤና አገልግሎቶች ካሉ፣ አገልግሎት የት እንደሚሰጡና መቼ እንደሚሰጡ ማወቅ
- አቅጣጫ ሰሜን፣ ደቡብ

## የትምህርት ተቋማት

- ትምህርት ቤቶች
- የጎልማሶች ት/ቤት /ካለ/

## የሃይማኖትና ማህበራዊ ተቋማት

ቤተክርስቲያናት፣ መስጊዶች፣ ሌሎች በሃይማኖት መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ ሰዎች በአብዛኛው የሚገናኙባቸውና የሚሰባ ሰቡባቸው ቦታዎች፣

## የልማት እንቅስቃሴዎች

- የመንግሥት መ/ቤቶች፣
- ሴቶች የሚሰባሰቡበት፣
- ሌሎች የልማት አውታሮች የሚገኙበት፣
- አናፂዎችና ኮንትራክተሮች የሚገኙበት፣
- የውሃና የጽዳት ስራ ፕሮጀክቶች፣
- የደን ልማት ፕሮጀክቶች፣
- የወፍጮ ማሽኖች ያሉበት፣




ስዕል 15. በምሳሌነት የቀረበ የመንደር ካርታ

# ክፍል 4

## ዓይን ማዝን (ትራኮማን) ለመቆጣጠር የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት

4.1. የዓይን ክዳን ቀዶ ህክምናን ለማካሄድ የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት

4.2. ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት ለመስጠት የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት

4.3. የፊት ንፅህናን ለመጠበቅ የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት

4.4. አካባቢን ለማፅዳትና ለማሻሻል የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት




ከዓይን ማዝ ለመላቀቅ በሚደረገው ጥረት አራቱን ዋና ዋና ስልቶች (ማመንን) በመጠቀም የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት

ስዕል 16. የዓይን ማዝን ለመቆጣጠርና ለመከላከል በሚደረጉ ፕሮጀክቶች የህብረተሰቡ ድጋፍ ወሳኝ ነው።

# ክፍል አራት

## የዓይን ማዝን (ትራኮማ) ለመቆጣጠር የህብረተሰቡ ተሳትፎ

**መግቢያ:-** በዓይን ማዝ በሽታ ቁጥጥር ፕሮግራም የህብረተሰቡን ተሳትፎ/ድጋፍ ማግኘት ቀላል ላይሆን ይችላል። ሆኖም ግን የሚከተሉትን ተሞክሮዎችና ልምዶች መሰረት በማድረግ የራሳችንን ስልት መቀየስ አለብን።

## 4.1. የዓይን ክዳን ቀዶ ህክምናን ለማካሄድ የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት




**ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች**

- ቀዶ ህክምናውን መፍራት ፣
- በቀዶ ህክምናው ችግራቸው እንደሚቀረፍ አለማወቅ ፣
- ህሙማንን ወደ ጤና ድርጅት ለመውሰድ የመጓጓዣ እጥረት መኖር ፣
- የገንዘብ እጥረት መኖር ፣
- በኦፐሬሽኑ መጠራጠርና እምነት አለማሳደር ፣
- እንደ ዓይን ሞራ መገፈፍ ይኼኛው ቀዶ ህክምና የማየት ችሎታን ይመልሳል ብሎ አለማመን ፣
- የቀጠሮ ቀን በጤና ድርጅቶቹ አለመጠበቅና በተደጋጋሚ መመላለስ ናቸው።

| |
|---|
| በአካባቢያችሁ የቀዶ ህክምናውን ለማካሄድ የሚከሰቱ ችግሮች ምንድናቸው? |

**መፍትሄዎች:-**

እዚህ ላይ የተቀመጡት የመፍትሄ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚሆኑት ቀዶ ህክምናውን የሚሰራ ሰው እስካለ ድረስ ሲሆን ከሌለ ግን የመጀመሪያው እርምጃ መሆን ያለበት ቀዶ ህክምናውን የሚሰራ ሰው ማሰልጠን ነው።

- ቀዶ ህክምናውን በተቻለ መጠን ለህመምተኞቹ መኖሪያ ቤት በሚቀርብ ቦታ መስራት ይህ ደግሞ ብዙ ህመምተኞችን የማግኘት እድል ይፈጥራል።
- የመጀመሪያዎቹ የቀዶ ህክምና ሥራዎች ስኬታማ መሆን አለባቸው ምክንያቱም ህሙማን በውጤቱ ከተደሰቱ ሌሎች ሰዎችም ለቀዶ ህክምናው እንዲመጡ ጥሩ ማስታወቂያ ይሆናልና።
- የባህል ህክምና አዋቂዎች ቀዶ ህክምናው የሚያስፈልጋቸው ሰዎችን ወደ እናንተ ሊልኩ ይችላሉ። ስለሆነም የቀዶ ህክምናው የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ምን እንደሚመስሉ ማሳየትና ወደነሱ ሲመጡ እንዲልኩ መጠየቅ ያስፈልጋል።


- የዓይን ቆብ ቀዶ ህክምናውን ልትሰሩ ስታስቡ ቀደም ብላችሁ መቼ እንደሆነ በእርግጠኛ ነት ለአካባቢው አመራር አካላትና ድርጅቶች ማሳወቅና እነሱም ለህብረተሰቡ እንዲነግሩና ቀዶ ህክምናው የሚያስፈልጋቸው ሰዎችን እንዲያዘጋጁ ማድረግ ተገቢ ነው::
- ሰዎች በቀጠሮ መስተጓጎል ምክንያት ከተቀየሙ በድጋሚ ላይመጡ ስለሚችሉ ቀጠሮን ማክበር ይስፈልጋል::
- የተሳካ የዓይን ማዝ የቀዶ ህክምና አገልግሎት መስጠት ሰዎች የበለጠ ለሌላ የዓይን ማዝ ቁጥጥር ተግባር እንዲሳተፉ ይጋብዛል::

**በአካባቢያችሁ በቀዶ ህክምናው የህብረተሰቡን ድጋፍ ለማግኘት ያስፈልጋሉ የምትሏቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ምንድን ናቸው?**




ስዕል 17.

## 4.2. ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት ለመስጠት የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት




### ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች

- የቴትራሳይክሊን 1% የዓይን ቅባት በቀን ሁለት ጊዜ ለስድስት ሳምንት የሚሰጥ በመሆኑ ይህ አዝጋሚ የህክምና አሰጣጥ ለሰዎች አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል::
- ህፃናት ቅባቱ ዓይናቸው ውስጥ እየተጨመረላቸው ለመቆየት አይታገሱም::
- ቅባቱ በሚደረግበት ጊዜ ሊያቃጥላቸው ይችላል::
- አንዳንድ ሰዎች ብዥ የማለት ስሜት ይፈጥርብናል ሊሉ ይችላሉ:: ሌሎች ደግሞ መድሃኒቱ ፈጣን ለውጥ አላመጣም ብለው መጠቀም ሊያቋርጡ ይችላሉ::
- መድሃኒቱ ላይገኝ ይችላል::
- መድሃኒቱ ሊወደድ ይችላል::
- ሰዎች ትንሽ ለውጥ ካዩ ሊያቋርጡት ይችላሉ:: አንዳንዶቹም እንደ ዋና ህክምና አይመለከቱትም::

- አንዳንድ ጊዜ መድሃኒቱ በትክክል አይደረግም። ለምሳሌ በቅንድብና በሽፋሽፍት ላይ ሊያደርጉት ይችላሉ።
- ሰዎች መድሃኒቱን ከተጠቀሙ በኋላ ሌላ ጊዜ ዓይን ማዝ ሲይዛቸው በመድሃኒቱ አመኔታ የማጣት ሁኔታ ይኖራል።
- የመድሃኒቱ ክዳን ሊረሳ ይችላል።
- ለቤተሰብ አባላት በሙሉ አንድ የቴትራሳይክሊን ቅባት እቃ ብቻ መጠቀም ለበሽታው መዛመት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል።

**በአካባቢያችሁ ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒቱን ለመጠቀምና የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማግኘት ምን አይነት ችግሮች ይኖራሉ?**

## መፍትሄዎች

- ለእናቶችና ለአካባቢ ጤና ተጠሪዎች ጊዜ ወስዶ ስለ መድሃኒቱ አጠቃቀም በደንብ ማስረዳት ህክምናውን እስከ መጨረሻ መከታተል ያስፈለገበት ምክንያት ምን እንደሆነ እንዲያውቁቱ ማድረግ፣ በዓይን ማዝ ምክንያት ዓይነ ስውር ከመሆን ይልቅ መድሃኒቱ የሚያስከትለው የዓይን መቆጣትና ብዥ ማለት የተሻለ መሆኑን ማሳወቅ፣
- የዓይን ቅባቱ እንዴት እንደሚጨመር ለእናቶች በትክክል ማሳየትና እራሳቸው እንዲሞክሩ ማድረግ፣
- መድሃኒቱን ህፃኑ ማታ ከመተኛቱ በፊት መጨመር ከሁሉም የተሻለ ጊዜ መሆኑን ማሳወቅ፣
- በቆላማና በረሃ አካባቢዎች መድሃኒቱ ስለሚቀልጥ በተቻለ መጠን ቀዝቀዝ እንዲቆይ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ለቤተሰቡ አባላት መድሃኒቱን ብቻ መጠቀም በቂ እንዳልሆነና የፊት ንፅህናን መጠበቅም እንደሚያስፈልግ ማስረዳት።
- ለምን መድሃኒቱ ለረጅም ጊዜ መደረግ ወይም መጨመር እንዳለበት ማስረዳት።

**ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒቶቹን በትክክለኛው መንገድ ለመጠቀም በአካባቢያችሁ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?**



ስዕል 18.

## 4.3 የፊት ንፅህናን ለመጠበቅ የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት



ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች:-

- የውሃ እጥረት መኖር ፣
- እናቶች ካለባቸው የሥራ ጫና የተነሳ የህፃናት ልጆች ፊትን ሁልጊዜ ለማጠብ ይቸገራሉ፣
- ሰዎች በአብዛኛው የፊት ንፅህናን መጠበቅ የሚሰጠውን ጠቀሜታ አይገነዘቡም፣

| |
|---|
| በአካባቢያችሁ የፊት ንፅህና አጠባበቅ ትምህርትን ለማስረፅ ያሉት ችግሮች ምንድ ናቸው? |



ስዕል 19.

መፍትሄዎች

- የህፃናትን ፊትና እጅ በንፅህና ለመጠበቅ ብዙ ውሃ እንደማያስፈልግ ማስረዳት ጠቃሚ ነው:: ውሃውን ለመቆጠብ ቀዳዳ ያለው የውሃ መያዣ ጣሳ ወይም ፕላስቲክ በዛፍ ላይ በማንጠልጠልና እንዲንዲጠባጠብ በማድረግ አነስተኛ ውሃን በመጠቀም የህፃናትን የፊትና የእጅ ንፅህናን መጠበቅ እንደሚቻል በደንብ ማስረዳት፣
- የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎችን /እናቶች፣ ሴቶች፣ ቤተክርስቲያናት፣ ት/ቤቶችና ጤና ተጠሪዎችን/ በመጠቀም የፊት ንፅህናን የመጠበቅ ልማድ በህበረተሰቡ እንዲዳብር ማስተማር፣
- እናቶች የሚገናኙበትን መድረክ በመፍጠር እንዴት በቀጣይነት የፊት ንፅህና መጠበቅ እንደሚችሉ እርስ በርስ ማወያየት፣


**በአካባቢያችሁ የፊት ንፅህናን ለመጠበቅ መፍትሄ የምትሏቸው ምንድናቸው?**



ስዕል 20.

1. ትንሽ ባሳ ወይም ፕላስቲክ ማግኘት
2. በዕቃው መቀመጫ ላይ ቀዳዳ ማውጣት
3. ዛፍ ላይ ማንጠልጠል
4. እናቶች እቃው ውስጥ በቀን አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ውሃ መጨመር
5. በቀዳዳው በሚንጠባጠበው ውሃ ህፃናት ፊታቸውን እንዲታጠቡ ማድረግ
6. በሚንጠባጠበው ውሃ ስር አትክልት መትከል
7. አትክልቱ ካለማና የውሃ እጥረት ከገጠመው ህፃናቱም በዓይን ማዝ እንደሚሰቃዩ ማሰብ

## 4.4. አካባቢን ለማፅዳትና ለማሻሻል የህብረተሰቡን ድጋፍ ማግኘት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች



- ህብረተሰቡ ችግሮቹን ለይቶ ላያውቅና የተለያየ የትኩረት አቅጣጫ ሊኖራቸው ይችላል፣
- ሰዎች ለብዙ ዓመታት ሲጠቀሙበት የነበሩትን ነገሮች መቀየር አይፈልጉም፣
- በህብረተሰቡና በልማት ሰራተኞች መካከል መግባባት ላይኖር ይችላል፣
- የሙያተኛ እጥረት ሊኖር ይችላል:: ለምሳሌ የመፀዳጃ ቤት እንዴት እንደሚገነባ የሚያውቅ ባለሙያ አለመኖር እንዲሁም
- የጊዜ እጥረት ሊኖር ይችላል፣

> አካባቢን ለማሻሻልና የህብረተሰቡን ድጋፍ ለማግኘት በአካባቢያችሁ እንቅፋት የሆኑት ምንድናቸው?

## መፍትሄዎች

- የአካባቢ ልማትና መሻሻል ለማምጣት ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በቅንጅት መስራት ለምሳሌ ከውሃ፣ ከአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ፕሮግራሞች፣ ከእርሻና ከትምህርት ድርጅቶች ጋር በመሆን መሥራት ይቻላል።
- እንደ ሃይማኖት መሪዎችና መምህራን ያሉ ታዋቂ ሰዎች ድጋፍ እንደሚሰጡ ማረጋገጥ፣
- አካባቢን በማሻሻልና በመቀየር የዓይን ማዝ በሽታን በማጥፋት ሰዎች ቀደም ብለው የሚያውቁትንና የሚተገብሩትን እንዲሁም አሁን ማድረግ ያለባቸውን የሚያጠናክር ትምህርት መስጠት፣
- እነዚህ መሻሻሎችና ለውጦች እንዴት መምጣት እንዳለባቸው ውሳኔውን ለህብረተሰቡ መተው፣
- በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን እውቀት ማስተባበር፣ የሰው ኃይልና ማቴሪያል መጠቀም፣
- የአካባቢ መሻሻልና ለውጥ የዓይን ማዝ በሽታን ለመቆጣጠር ከምናደርጋቸው ተግባራት ውስጥ በጣም አስቸጋሪና ውስብስብ በመሆኑ በእርጋታ መንቀሳቀስ፣

> የአካባቢ ልማትና መሻሻል ለማምጣት ምን አስተያየት አላችሁ?



ስዕል 21.

# ክፍል አምስት

## የአገራችን የዓይን ማዝ (ትራኮማ) በሽታ ስርጭት

### እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ደረጃ አመዳደብ

1. እድሚያቸው ከ1-10 ዓመት ከሆኑት የህብረተሰቡ ክፍሎች ውስጥ ቀላልና ከባድ የዓይን መለብለብ ያላቸው (TF and/or TI) ከ20 በመቶ በላይ ከሆኑ፣
2. እድሚያቸው 40 ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሴቶች የላይኛው የዓይን ክዳን መቀልበስ ያለባቸው ከ1 በመቶ በላይ ከሆኑ

የዓይን ማዝ በሽታ በህብረተሰቡ ውስጥ እንደዋነኛና አንገብጋቢ የጤና ችግር ተደርጎ መወሰድ አለበት::

በሀገራችን ቁጥራቸው አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ዓይነ ሥውራን እንደሚኖሩ ይገመታል:: ከነዚህም ውስጥ 40% የሚጠጉት በዓይን ማዝ ምክንያት ለዓይነሥውርነት የተዳረጉ መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል:: በሀገራችንም በቅርቡ ለአብነት ያህል በደቡብ ጎንደር በሚገኙ አራት ወረዳዎች (እብናት፣ ደራ፣ እስቴና ስማዳ) በታህሳስ ወር 1993 በተሠራ ጥናት የዓይን ማዝ በሽታ በከፍተኛ ሁኔታ ተንሠራፍቶ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል:: ይህም በአካባቢዎቹ በሽታውን ለመቆጣጠርና ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት መደረግ እንዳለበት የሚያመላክት ነው::

የሚከተለው ሠንጠረዥ የጥናቱን ውጤት ያመለክታል፥

| | እብናት | እስቴ | ደራ | ስማዳ |
|---|---|---|---|---|
| ቀላልና ከባድ የዓይን መለብለብ (TFTI) (1-10 ዓመት የሆኑ ልጆች) | 94.7% | 90.2% | 81.2% | 84.7% |
| የላይኛው የዓይን ክዳን መቀልበስ (TT) (ዕድሚያቸው ከ39 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች) | 20.3% | 18.3% | 23.2% | 18.6% |

እነዚህ የተገኙት ውጤቶች የህብረተሰቡን ጤንነት ለመጠበቅና በሽታውንም ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱትን አራት ዋና ዋና መንገዶች [ማመንን (SAFE)]መጠቀምና ተግባራዊም ማድረግ ወሳኝ መሆኑን ያመለክታሉ::

The Carter Center

Lions Clubs International

የአማራ ክልል ጤና ቢሮ
Amhara Regional Health Bureau

በካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ የተዘጋጀ
ጥቅምት 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

EDM Printing Press